# ልጅነቴ !
# ማርና ወተቴ !!

## ከፍቱን ጣጣቴ

**ምን** ልትለኝ እንደሁ እንጃ ! ትዝ አለችኝ ልጅነቴ !
ደግማ ደጋግማ ታይታኝ ውልብ አለች ከፊቴ ፧
ትዝታዬን ልትነግረው መሰለኝ ለእም-አበውነት ሕይወቴ ፧
የልጅነት ሕይወቴ ያቺ ጥንቅሽ ያቺ ለጋ !
ለዓለም ችግር ሠቆቃ የማትሰጠው ዋጋ !
በውል ለማታውቀው ጦርነት ፧
ጥበብ ላልሆነ ጅልነት ፧
ለረሃብና ሽነፈር ለሕማምና ስደት ፧
ለሰይጣናዊ ምቀኝነት ፧
ለአልጠግብ ባይ ሆዳምነት ፧
ለተጃጃለ ኀሠኖነት! ለአጥፍተህ ጥፋ ዕኩይነት !
ልጅነቴ ምንም ግንዛቤ አልነበራትም በውነት !!

የፍቀር ምንጭ የነበረች ያቺ የልጅነት ሕይወቴ !
ዕኩይነት የሌለባት ደስታን የምታመነጭ ለኔነቴ !
ቂም በቀል የሌለባትና እንደ ወንዝ ቄጠማ የለሰለሰች !
እንደ ጽጌረዳ አበባ ትርክክ ብላ ያማረች !
ውስጧን በሳቅ ደስታ ተሞልታ ! እንደ ማር የጣፈጠች !
ዳግመኛ ላትመጣ እንደ ጤዛ የነጠፈች ፧
አሁን ከየት ልትገኝ ነው ? ከፊቴ ድቅን ውልብ ያለች ?
በመኖር መኖርን ኖሬ ሕይወቴ ደስታ ተትረፍርፏት ፧
ጣፋጭዋ ልጅነቴ ያለሃኬት የኖርሁባት ፧
ወተቴን እስከ ኀልፈቴም አልረሳት !!
የእም-አበውን ዓለም ተዉት ዓለም ማለት እሷ ናት !
ተስተውሎ ቢኖረውም የእም-አበው ሕይወት ጉዞ ፧
ቁጣ ንዴት ግንፍልነት ምቀኝነትን አርግዞ !
በቅናት አምባጓሮ እርስ-በርሱ ተጠዛጥዞ !
በመጠላላት በቀል አንዱ ሌላውን መርዞ 1
ሥቃይ ትካዜ ሃሳብ ጭንቀት የማይለቀው ፧
መከራ የበዛበት የእም-አበው ሕይወት ብቻ ነው !!

ከቢጤዎቼ ጋር ኩኩሉ ድብብቆሽ የተጫወትነውን !
ተራግጠን አቧራ ያቦነንንበትን !
ጭቃ ያቦካንበትን ውሃ የተራጨንበትን !
ጅራፍ የተወናጨፍንበትን !
ኳስ የተራገጥንበትን !
በልፊያ ወድቀን የተነሳንበትን !
ትዝታዋን ይዛ በዓይነ ኅሊናዬ መጣች ልጅነቴ ፧
ማርና ወተቴ !
ጣፋጭ መራሩን ዓለም እንዳገናዝብ በሕይወቴ ፧
በድንገት በቀ ብላ ድቅን አለች ከፊቴ !
ከጣፋጭዋ ልጅነቴ አንድ ነገር ትዝ አለኝ ፧
የምወደው የሚወደኝ ጥሩ ጓደኛ ነበረኝ !

እሱ ከሀብታም ቤተሰብ ፤ እኔ ከድሃው ብፈጠርም !
ጣፋጭ ልጅነታችን አልከፋፈለችንም !
እሱ መልካም ዳቦ ፤ ከረሜላ ብስኩት ሲያመጣ !
እኔም እንዳቂሚቲ ቆሎ ቂጣ !
የተገኘውን ተካፍለን ፤ በልጅነት ጨዋታችን ረክተን !
ውስጣችን በደስታ ተሞልቶ ! እየፈነደቅን ሳለን ፤
ከመራራው የእም-አበው ሕይወት አንድ ነገር ተከሰተ ፤
የጓደኛዩ እናት አፍጥጠው መጡ ልጁም ተርበተበተ ፤

ከነዚህ እከካም ልጆች ጋር አትጫወት አላልኩህም ?
የበቆሎ ቂጣ እከክ እንደሚያስይዝ አልነገርኩህም ?
እስቲ ተመልከተው ልብስና ጫማህን !
ፀጉርህ ላይ ያለውን አቧራ አመዳሙ ፊትህን ፤
አሁን አባትህ መጥቶ  በልምጭ ሳይገርፍህ ፤
ትሄዳለህ አትሄድም ወደቤትህ ?

ብለወ ተቆጡ ልጃቸውን እማማ !
እሱም ለጊዜው ፈርቶ ሸሸ እያቅማማ ፤
ያሻቸውን ቢሉ እማማ ! ይሉኝታ ሀፍረት ባይገባቸው ፤
ቁጣን ለጊዜው ቢሸሽ የሚወዱት ልጃቸው ፤
ጣፋጭ ልጅነታችን ያቺ ጥንቅሽ ያቺ ለጋ !
ለመራራው የእም-አበው ሕይወት ሳትሰጠው አንዳች ዋጋ ፤
ዞሮ መጣ ጓደኛዩ ማርና ወተቴ ተጣርታው !
በብሩሁ ዓለማችን ተጀመረ ጨዋታው !

መሸ-ነጋ ሌት ተቀን ተቆጠረ ፤
ዓመት በዓመት ተቀየረ ፤
መንግሥትም በመንግሥት ተዘወረ ፤
መሬት ላራሹና ፤ የከተማ ቦታና ቤት ዓዋጅ ታወጀ ፤
የነቃው ሊንገለጀጅ ! ያልነቃው ሊነቃ ተዘጋጀ !
አቤት ሽርጉዱ አዲስ መንግሥት ሲመጣ !
አዲስ ዕቃ ሲያስገባ አሮጌ ዕቃ ሲያስወጣ !
የበቀል ሰይፍ ሲመዘዝ ሰው ያለፍርድ ሲቀጣ !
ዕቃ በዕቃ ሲቀየር ፤ ዕቃን ሲተካው ዕቃ !
ይኸው ሆነ አዲስ ሥርዓት አከተመ አበቃ !!

ሹም ሽር እየተባለ ሰው ያለ ኃጢአቱ ሲወገዝ ፤
የሥልጣን ጥመኛ ሩጫ እንካ በእንካ ሲታገዝ ፤
አንዱ በጭካኔ ሲገደል ! ሌላው በወኅኒ ሲታጎር !
ሌላውም ለስደት ሰለባ ሆኖ ፥ ካገር ከቤቱ ሲባረር !!
ያው ዞሮ ዞሮ ያንኑ የተጨቆነ ሕዝብ ለመግዛት !
በጠመንጃ ለማማቀቅ አንደበቱን ለመዝጋት !
አፍኖ ለማኖር ነው ዲሞክራሲን እንዳይለብሳት !
ሕዝብ በሰላም እንዳይኖር ፤ ጦርነት እንዳይገታ ፤
ጠኔ ሰቆቃው እንዲባባስ እንዳይቋረጥ ዋይታ !
የሀገር አንጡራ ሀብት በውጭ ኃይላት እንዲዘረፍ !
ድኅነት እንዳይገታ ኀልውናው እንዲገፈፍ !
አቤት ሽርጉዱ አዲስ መንግሥት ሲመጣ ፤
አዲስ ዕቃ ሲያስገባ ፤ አሮጌ ዕቃ ሲያስወጣ ፤
የበቀል ሰይፍ ሲመዘዝ ሰው ያለፍርድ ሲቀጣ ፤
ዕቃ በዕቃ ሲቀየር ፤ ዕቃን ሲተካው ዕቃ !
ይኸው ሆነ አዲስ ሥርዓት አከተመ አበቃ !!

አሮጌ ሹማምንቶች ተወግደው ፤ አዲሶቹ ቢፈጠሩ ፤
ለውጣችን አምሮበተ አያውቅ ፤ አይካድ ታሪክ-መዘክሩ !
ዕቃ በዕቃ ሆነና ነገሩ !!
ለማንኛውም እማማም እያረጁ !
በአዲሱ ሥርዓት ሊንገለጀጁ !
የገጠር-ከተማ ሀብታቸው ተወረሰ !
ባለቤታቸውም ሥራ አጡ የገቢ ምንጭም አነሰ ፤
እኔና ጓደኛዬም አድገን ለአኢወማ ስንበቃ ፤
የወቅቱን ሥርዓት ተከተለን ስንነቃና ስናነቃ ፤
ጊዜው ግድ ብሎን ሥርዓቱን ተቋደስን !
ሀገር ታድጋለች ስላሉን ብቻ የሆነ መስዋዕትነት ከፈልን !

ከዕለታት አንድ ቀን እማማን ከቀበሌ አገኘኋቸው ፤
ከአክብሮት ሠላምታ ጋር ምን ያደርጋሉ ? አልኳቸው ፤
“ ምን አደርጋለሁ ብለህ ጌትዬ ለራሺን ነው የመጣሁ !
መከረኛው የበቀሎ ወረፋ እስኪደርሰኝ ነው የጠበቅሁ !
አሻጥረኛው ነጋዴ ዋጋውን አንሯል !
ማን መሸመት ይችላል ?
አይ ልጄ ጉደኛ ሕይወት ላይ ነው የደረስን !
ማደግ መሻሻል ቀርቶ የዝቅዝቅ ነው የወረድን !!
የለፋህበትን ሀብትህን ከተነጠቅህ !
ምኑን አለሁ ትላለህ ? “

አሉ እማማ የነበርንበተ ሥርዓት አማሯቸው !
የሚያደርጉትም መላው ጠፍቷቸው !
ግን እከክ ስለሚያስይዘው በቀሎ ያኔ ያሉትን ዘነጉ እማማ !
አልስቅ አላለቀስ ተጨንቄ ነፍሴ በውስጤ ተደምማ !
ያሳደገኝን በቀሎ እኔ የድሃው ልጅ ባልረሳውም !
የጓደኛዬ እናት ናቸውና እማማ ላይ ቂም አልይዝም !

አሁንስ ምን ብለው ይሆን እማማ ?
ሀገር ብርሃኗ ጠፍቶ ሲዳረግ ለጭለማ !
ሰብዕና ሲናቅ ሲረገጥ ፤ ባሻ አዳሪዎች ሲፎክሩ ፤
ዓለማችን በወሮበሎች ታጥራ ድሆች በግፍ ሲወገሩ !
አሁንስ ምን ብለው ይሆን እማማ ?
ከደርግ የባሰው የሰይጣን ሹም ልባቸውን ሲያደማ !
እማማ የአፍ ወለምታ ሲያድጣቸው ፤
በቀሎ እከክ ያሰይዛል ነበር አባባላቸው !
በቀሎው እንደሚያስደገድጋቸው ፤
ከቀበሌ ሱቅ እንደሚያስቀማቸው ፤
ከቀድሞው አውቀውት ቢሆን ያንን ምሥጢር ፤
ትንፋሽ አይወጣቸውም ነበር !!
ወያኔዎችም እንደ እማማ ምሥጢሩ ቢርቃቸው ፤
ንቀት-ጥጋብ- ትዕቢቱ ዛሬን ቢያስፈነድቃቸው !
ኀልፈት የማይነካቸው ቢመስላቸው ፤
የሕዝብ ኃያልነት ባይገባቸው !
በነገው ዕይታ  ግን ሌላ ነው ነገሩ ፤
ይገለጣልና የውድቀታቸው ምሥጢሩ ፤
አፋቸውን አድጦታልና ለነገው ወዮላቸው ፤
ቢወዱም ባይወዱ ውድመት ነው የሚጠብቃቸው ፤
ከፋፍለህ ግዛው ያበቃል ከንግዲህ መድረክ የላቸው ፤
የሚዋሹ የሚነጥቁ የሚዘርፉ የሚገድሉ !
ምን ይውጣቸው ይሆን ያሸነፈ ዕለት ባለድሉ ?

ባለድሉ የምለው ፤ ባለድሉ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው !
ጉሮ ወሸባዬ ! የሚባልለት የነገ  አሸናፊነቱን የማልጠራጠረው !
በርግጥ አሸናፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው !

ልጅነቴ ማርና ወተቴ !
ቅንነትን ልታስታጥቀኝ ነበር ድቅን ያለች ከፊቴ !
ጅልነቱን የጎሣ ሸንኮፍ እንዳወልቅ !
ከሀገሬ ልጅ ከወገኔ ጋር እንድታረቅ !
መራሩን ዓለም አስወግጄ ጣፋጩን ዓለም እንድተካ !
የዛሬውና መጪው ትውልድም በደስታ እንዲረካ !
መራሩን የእም-አበውነት ሕይወት እንዳጣፍጥ !
የመጠላላት ሕይወትን ወደ ፍቅር እንድለውጥ !
ተንኮል የሌለበትን ፖለቲካ እንዳራምድ ፤
የውስጥና የውጭ ጠላቴን እንዳዋርድ ፤
የቅንነት መልዕክቷን ልተገብር በምችለው እጥራለሁ ፤
ያችን ጣፋጭ ልጅነቴን ዛሬም እወዳታለሁ ፤
ዳግም ባላገኛት እንኳ ሁሌም አስታውሳታለሁ !
ጣፋጭ ወተቴን እንዴት አረሳታለሁ ?
እንደ ልጅነታችን ጊዜ ወገኖች ሁሉ ቅን ሁኑ ፤
ቅንነት ያቀራርበን በአንድነታችን እመኑ  ፤